# እኛ በኛ እንኩራ

እንደ ትላንትናው ፣ እንዳባቶቻችን
ከመሃል ከተማ ፣ እስከ ጠረፋችን
ካመፀኞች ጋራ ፣ ይጀመር ፍልሚያችን
ምንሽር ጓንደውን ፣ ያጨኸው ህዝባችን ።

አገሬ ኢትዮጵያ ፣ ቴዎድሮስ ያደገባት
ጋራው ሸንተረሩ ፣  ታሪክ የሰራባት
ሜዳ መስኮት ዛሬ ፣ ባንዳው ፈነጨባት ።

ሞቅ ሞቅ አድርገው ፣ ወያኔ ይሸበር
ትንፋሽ አሳጥረው ፣ በማሰው ይቀበር ።

ለእናት ኢትዮጵያ ፣ ባንድነት ዝመቱ
ትርጉም አልባ ፣ እንዳይሆን አገሬ ማለቱ
ግደታን መወጣት ፣ ይሁን እንደጥንቱ
ሬሳን ይመስል ፣ ይብቃ መጨመቱ ።

ሁሉም ጦሩን ያንሳ ፣ ጠላት ላይሆን ወዳጅ
ሉአላዊነቱን ፣ ያስከብር በግዳጅ ።

ጀግና የጀግና ልጅ ፣ የሃገር አለኝታ
ግንባሩን የሚሰጥ ፣ ሳይፈራ ላንዳፍታ
ና ግጠመኝ የሚል ፣ ሞልቶ በየቦታ
ውድ የሚሞትላት ፣ አገሬ መች አጥታ ።

ህጻን ሽማግሌ ፣ ወጣት ወንድ ሴቱ
ዝናን ያተረፈ ፣ ዛሬም እንደጥንቱ
ባገሩ የሚኩራ ፣ ቆፍጣናና ብርቱ
ችግር የማይፈታው ፣ የጥንት የጠኋቱ
ንቅንቅ የማይለው ፣ ቆርጧል አንዴ ሃሞቱ ።

ያሳለፍነው ይብቃ ፣ ጠንክረን እንስራ
ሸክማችንም ይቅለል ፣ እኛ በኛ እንኩራ
ንፋስ ሳይገባብን ፣ ባንድነት በጋራ
ፋኖው ተነሰና ፣ ጓዶችህን ጥራ
ልክህን አሳየው ፣ ለባንዳው ኩታራ ።

ታዛቢው